# ይድረስ ለሻማ ብርሃኖች

ሰለሞን ሞያ 02/11/09

በቅድሚያ እንደምን ናችሁ? ስለእናንተ ለመናገር የተለያየ የመግቢያ ርእስ ተጠቅሞ መፃፍ የሚቻል ቢሆንም እኔ ካለኝ አቅም ስለ እናንተ ሙሉ በሙሉ ለመናገር ካለኝ የሞያና ችሎታ ዕጥረት የፈለኩትን ያክል የልቤ ትርታ መናገር አልቻልኩምና ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም ነው እና የቋጠርኳትን ሳደርሳችሁ ያላችሁበትን የገነት ሰፈር የለመለመ እንደሆነ በመተማመን ነው፡፡

መቸስ እናንተን የሻማ ብርሃኖች ብዬ ለምን ፅሑፌን እንደጀመርኩት እንደሚገባችሁ ተስፋ አደረጋለሁ ፡፡ ምክንያቱም ሻማ የሰው ልጅን ብርሃን ለመስጠት እራስዋን ተቃጥላ የምታልቅ ናት፡፡ በመሆኑም እናንተ አለቃችሁ እያልኩኝ አይደለምና፡፡ ይልቁንስ እናንተን በሻማ ምሳኔለት ጠቀስኳችሁ ጠቀሰኳችሁ እንጂ የናንተ አጥንትና ደምስ አሁንም በከፍተኛ ደረጃ ሥራ ላይ እንደሆነ እናንተም የምትዘነጉት አይደለም፡፡

ይልቁንስ ለመግለፅ የፈለግሁኝ እናንተ ከምትናፍቋቸው ቤተሰቦቻችሁ እንዲሁም ከሚሚሙቀው ኑሮአችሁ ተለይታችሁ በረሃ ላይ ስትወጡ መስዋዕነት እንደሚሆንና አልያም አካላችሁ እንደሚጐድል ቢሆንም ግን ለተቀረው ህዝብ መብራት ሆኖ እንደሚበራና የተጐሳቆለው የህዝብ ኑሮ እንደሚሻሻል ታሳቢ በማድረግ ነበረ፡፡ ዓላማችሁ ሙሉ በሙሉ የመሳካቱ ፍሬ ደግሞ በየአቅጣጫው እየተመዘገበ ያለው ውጤት በፍጥነቱና በፍትሐዊነቱ ህዝቡ ፍላጐቱን የሚሟላለት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ ተግባራችሁ ደግሞ በሰማዕትነት ቦታ ተቀምጣችሁ በየዓመቱ ሃገራችሁ የምታስመዘግበው የለውጥ ሂደት እያያችሁ እንደምትሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ምንአልባት ግን ዛሬ ለመናገር የፈለኩኝ እናንተ አታውቁትም ብየ ሳይሆን የ35

ዓመት የካቲት 11 የወርቅ እዮቤልዩ በዓል ለማክበር በምንዘጋጅበት ወቅት የምንገኝ በመሆኑ ማን ምን እየሰራ እንደሆነ ትንሽ ልጠቁማችሁ ስላሰብኩኝ ነው፡፡

እንደ ዜጋ ባለሁበት የስራ ዘርፍ ተሰማርቸ የአቅሜን ስሰራ እናንተ በተለያየ ወቅት በተደረጉ በመራራ  ውግያዎች ከጓዶቻችሁ ተለይታችሁ ሰማእት ስትሆኑ ተናገሩት ተብሎ በዒድ ሐቂ ሙዝየም ተፅፎ ያየሁት ፅሁፍ ሳስታውስ ሁሌ አእምሮዬ እንዴት እንደሚነቃቃና እንደ ዕድል ሆኖ ከጐናችሁ የተቀሩት በትጥቅ ትግሉ ድል በኋላ በተለያየ ሥራ ያሉ ጓዶቻችሁ ምን እየሰሩ እንደሆኑ እንዲሁም የናንተን አደራ ለመወጣት እራሴን ምን እየሰራሁ እንደሆነ እገመግማለሁ፡፡

ቃላችሁን አንዴ ልድገመው እና ወደ ግምገማየ ልግባ "ጓዶች እኔ በክብር ስሞት እናንተ ማዘን የለባችሁም፡፡ ይልቁንስ እያንዳንዱ ታጋይ ከድል በኋላ ጓዶቹህ የት ቀሩ  የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የት እንደሞትኩ፣ እንዴትና ለምን እንደሚትኩኝ ጠንቅቆ ማወቅ ትልቁ አደራ ነው!" የሚል ሲሆን በተለያየ መንገድ ተልእኮ ተሰጥቶት ሥራ ላይ ያለው በመንግስታዊ ተቋማት መልካም አስተዳደር በማስፈን እንዲሁም በግል ስራ ላይ ያለው ፣ የትጥቅ ትግሉ ለመደገፍ ከሕይወቱ እስከ ንብረቱ ለትግሉ መሳካት ክንድ በመሆን ያስረከበው ህዝብ እውነት ይሄን የአደራ ቃል ለመተርጐም ቀን ተሌት የተጠመደ መሆኑ ሳየው ሁለመናየ በሐሴት ይሞላል፡፡ ሌላ ቀርቶ በትጥቅ ትግሉ ላይ አካላቸው ያጡ በተቀረቺው አካላቸው ዓላማው ለማሰቀጠል የሚያደርጉት ጥረት ብትመለከቱ እውነት አሁንም የፀረ ድህነት ትግሉ ተጧጥፎ እየቀጠለ መሆኑን ለማሰታወስ እወዳለሁ፡፡

በጣም የሚገርመው ለእናንተ መንገሩ አዲስ ባይሆንም በሕይወቴ በጣም ያናደደኝ ነገር ደግሞ ልንገራችሁ፡፡ ንዴቴ ግን በቁጭት እየተናገርኩ ሳይሆን በእልህ የናንተን አደራ ግቡ ሙሉ በሙሉ እስኪረጋገጥ ድርስ በመሥራት መሆኑ ይገባኛል፡፡  ሆኖም ያለንበት ወር የካቲት አይደል?  ስለዚህ በየዓመቱ የገባንበት ቃል ምን ላይ ደረሰ ብዬ ከመገምገሜ በፊት ከሰማእት ሳወራ ንስሃ መግባት አለብኝ፡፡  በመሆኑም ተቀይሜአለሁ ለማለት ፈልጌ ነው፡፡

ደ.ጋግሜ ሳስበው ትግል ነው እና ሰዎች ተሳስተው ያልሆነ መአዝን እንደሚይዙ ይገባኛል፡፡ ሆኖም ግን ፅንፍ የረገ ትዕቢታቸው ሳያንስ ትናንትና "Tgrai to regain its dignity, It should done some thing to its stone" በማለት ካሁን በኋላ ትግራይ የሰሃራ በረሃ አካል እየሆነች በመምጣቷ የኢትዮጵያ አካል ሆነች አልሆነች አያሳስብም በሚል ህዝብና አካባቢ እንደጠላት በመፈረጅ በሰማይና በምድር ህዝቧንና መንደሮቿን አቅማቸው እስከፈቀደ ድረስ በማቃጠል የኢሰፓ የጥፋት ውሳኔ ካስወኑ ወንጀለኞች ጐን የተሰለፉ ጓዶቻችሁ ስትመለከቱ መስዋዕታችሁ እንዳያማርራችሁ አደራ እላችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም የሰማእታት ደም ረግጦ ሲወጡ በየተኛው ጎራ ላይ እንደሚሰለፉ የአቢታዊ ዲሞክራሲ ገምግሞ የጨረሰው ነው፡፡ እነሱ ያሉበት ቦታ በበሰበሴው ጭቃላይ  በመሆኑ የሚታዘንባቸው እነሱ ናቸው፡፡

ምክንያቱም ትናንትና በመሳላቅ ለተፋት አክታቸው ተመልሰው እየላሱት ይገኛሉ፡፡ እናንተ የወደቃችሁበት ዓላማ ግን በተለይ የተሃድሶ መስመር ተከትሎ በተነደፈው የነጠራ የአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ መስመር አርሶአደሩ፣ ምሁሩ፣ የከተማ ነዋሪው ወጣት፣ ሽማግሌ ሳይለይ የተሰለፈበት በመሆኑ በየዓመቱ የሚመዘገበው ውጤት ኢትዮጵያ በዓለም ፈጣን እድገት ከሚያስመዘግቡ አገሮች ተርታ ለመሰለፍ በቅታለች፡፡

ያ ሁሉ የሆኖው የእናንተው የሻማ መብራቶች የትጥቅ ትግል ለሚጠቀቅ ሂወት እደሰጣችሁ ሁሉ ዛሬም በየጋራውና ሸንተረሩ ያለው አጥንታችሁ የተተከሉ ዛፎችን በሁለት እግራቸው እንዲቆሙ ደግፌ በመያዝና ደማችሁ እንዳይጠሙ እያጠጡአቸው በመሆኑ እንዲሁም መላ የኢትዮጵያ ህዝብ ነጥሮ በመውጣት ውጤታማነቱ በተ.ጋገጠው የተሃድሶ መስመር የተሰለፉ በመሆናቸው ግለሰቦች ትናንትና የተፋትን ተመልሶ እየላሱ ናቸው በሚል ተሳስተው በቀለም አብዮተኞች ጐራ እንዲሁም በትምክህትና ጠባብነት በተጨማለቀ መስመር ገብቶ የሚከተላቸው እንደሌለ ላረ.ጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡  ይልቁንስ እኔን ጨምሮ ተቀይመናቸዋል፡፡

እንግዲህ ለዛሬው በዚህ ይብቃኝ እና በግንቦት ወር በሚደረገው ምርጫ ላይ ለመሳተፍ የኢትዮጵያ ህዝብ በህገ መንግሥት ያሰፈረውን የሥልጣን የበላይነት

መብት ለመጠቀም የመራጭነት ካርድ በመውሰድ ላይ በመሆኑ የዚህ ውጤት ይገኙላችሁ ግንቦት 20 ላይ እንዲምፅፍላችሁ በመተማመን ነው፡፡